# ዔሳዋውያን ክብረ ቢስ
# ክብራቸውን ሲሸጡ ለዕለት ጉርስ
## ከያዕቆብ አታላይ

የእናት ሆድ ዥንጉርጉር፦ ሰነፉ ዔሳውና ብልጣ ብለጤው ያዕቆብ መንታ ናቸው። << ያዕቆብ ወጥ ሠራ፤ ዔሳውም ደክሞ ከበረሃ ገባ፤ ዔሳውም፣ ያዕቆብን፦ ከዚህ ከቀዩ ወጥ አብላኝ፥ እኔ እጅግ ደክሜአለሁና አለው፤ ስለዚህ ስሙ ኤዶም ተባለ። ያዕቆብም፦ በመጀመሪያ ብኵርናህን ሽጥልኝ አለው። ዔሳውም፦ እንሆ እኔ ልሞት ነኝ ይህች ብኵርና ለምኔ ናት? አለ። ያዕቆብም፦ እስኪ በመጀመሪያ ማልልኝ አለው። ማለለትም፤ ብኵርናውንም ለያዕቆብ ሸጠ። ያዕቆብም ለዔሳው እንጀራና የምስር ወጥ ሰጠው፤ በላ፥ ጠጣ፥ ተነስቶም ሄደ፤ እንዲሁም ዔሳው ብኵርናውን አቃለላት>>። (ዘፍጥ. ፳፭ ፥ ፳፱-፴)

ከጥቅሱ አንድ ታላቅ ቁም-ነገር መማር ይቻላል። በተለይ ክብረ ቢስ ዔሳዋውያን ቅንጅቶች የኢትዮጵያ ሀገራችን ሀገራዊ ነጻነትና ብሔራዊ ክብር ለባዕዳን ኣሳልፈው ለመሸጥ መደሎታቸው በቀጥታ ዔሳው ክብረ-ብኵርናውን ለዕለት ጉርስ ብሎ ከመሸጡ ጋራ ማነጻጸር ይቻላል። እንዲያውም፦ ዔሳው ክብረ ብኵርናውን የሸጠው ለታናሽ ወንድሙ፣ ለያዕቆብ ነበር። ቅንጅቶች ግን አባቶቻችን በየጊዜው ከሩቁም ከቅርቡም የሚመጡባቸውን ወራሪዎች በጀግንነት ተከላክለው ያቈዩልንን ሀገር ለማስወረር ባዕዳንን እየጋበዙ እንሆ ልዑላዊነታችንን ውሰዱ እያሉ ለመሸጥ ሲዋዋሉ እያየን ነው። በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ሰዎች በፓርቲ ደረጃ ተደራጅተው ሀገር ሲክዱ አየን። ስለ ዚህ ቅንጅቶች <<የረመጥ ልጅ አመድ>> ሆኑ፤ ረከሱ፣ ዝቅ ዝቅ አሉ፣ ዘቀጡ፣ ተዋረዱ።

ዔሳው ክብረ ብኵርናውን ለወንድሙ ለያዕቆብ ሊሸጣት የቻለው፣ በማዛፉ ራብ ስለጠናበት ሳይሆን ይህች ብኵርና ለምኔ ናት በማለት ስለ ኣቃለላት መሆኑ በጥቅሱ ማሰርያ ዓንቀፅ ላይ ተሰምሮባታል። ሆዳሙ ዔሳው የአንድ ቀን ራብ ታግሦ ክብሩን ቢያስጠብቅ በተሻለው ነበር። ነገር ግን የሆዳም ሰው አንገት አዙሮ ማየት አይችልምና ዔሳው አዙሮ ማየት ተሳነው። ራቡንም ሊታገሠው ኣልቻለም፤ ባለመታገሡም እንሆ ክብሩን አጣት፥ ስሙ ሳይቀር ተለወጠ፥ ኤዶም ተባለ፤ ዔሳው ተዋረደ፥ ብኵርናውን ኣጣ። ከዚህ አድነኝ ያሰኛል፦ ታላቅ የነበረው ሰው ታናሽ ሆነ፥ ታች ወረደ፥ ዝቅ አለ።

ዔሳው ብኵርናውን እንደሸጣት፣ ቅንጅታውያን ዔሳዋውያንም ክብራቸውን በመሸጥ ላይ ናቸው። በተለይ H.R 2003 በመባል የሚታወቀው ሞግዚታዊ ወይም ቅኝ ግዛታዊ (Colonial bill) ረቂቅ አዋጅ (በUnited States Congress) በውጭ ኃይሎች ተዘጋጅቶ ይምጣልን እያሉ መጮሃቸው ራስን ማዋረድና የሀገርን ክብር መሸጥ ማለት ነው። በዚሁም ፖለቲካዊ ስብእናቸው እንደ አበባ ረግፏል።

የH.R 2003 ፖለቲካዊ ትርጉም፦ አጠር ባለ መልኩ ሕግ ኣውጡልን፣ ኑ ተቆጣጠሩን፣ (Come control us) እኛ እራሳችንን ማስተዳደር ኣንችልም፣ ነጻነት ኣስጠልቶናል፣ ባርነት ኣምሮናል ማለታቸው

ነው። ፈጥናችሁ ኑ የሀገራችንን ሉዑላዊነት ውሰዱ በማለት በኤውሮጳና በአመሪካ ወይም በኋይት ሃውስ አደባባዮች ወጥተው ቅንጅታውያን ነጻነታቸውን ለመሸጥ ገበያ እየፈለጉና እያፈላለጉ ናቸው።

በዔሳዋውያን ቅንጅታውያን ግብረ አበር በአመሪካም ሆነ ከኤውሮጳ በኩል ይህ H.R 2003 የተባለውን ቢል ለማውጣት መሞከር ማለት ደግሞ በኢትዮጵያ ውስጣዊ ጉዳይ መግባት እና በኢትዮጵያ ሉዓላዊነት ላይ ጣት መቀሰር ማለት ነው። ያ በኢትዮጵያ ልዑላዊነት እና ነጻነት ላይ ያልተቃጣ ባይሆን ኖሮ፣ ወይም የመተባበርና አለመተባበር ወይም እርዳታቸውን የመለገስና አለመለገስ ጉዳይ ቢሆን ኖሮ ሕግ ማውጣት አስፈላጊ አይደለም፤ <u>እመኒ እወ እወ፣ ወ እመኒ አልቦ ኣለቦ፣</u> ማለትም <u>Yes or No</u> ቢሉን በበቃቸው ነበር። ከዚህ በተረፈ የነሱ ሞግዚትነትን በማትቀበል ነጻና ለዘመናት ሉዑላዊነትዋን ጠብቃ በኖረችው ሀገራችን፣ በማያገባቸው በኢትዮጵያ ወስጣዊ ጉዳይ ላይ ገብተው ለማዘባረቅ፣ ወይም ሕግ ለማውጣት ደግሞ መብት የላቸውም።

ለሰነፉ ሰው ዔሳው ለጆች፣ ለቅንጅታውያን ወገኖቻችን ደግሞ በሚገባቸው የጌቶቻቸው ቋንቋ ነገሩን ላስጨብጣቸው። *(From political science point of view, if an Ethiopian support H.R2003 to pass. it is paramount to self-enslavement.)* ከዚህ ውጭ ሌላ ምንም ትርጉም የለውም፤ ሊኖሮውም ኣይችልም። ይህ ጉዳይ ጠለቅ ብለን በሀገራዊ ሉዓላዊነት (National sovereignty) ፖለቲካዊ ትንታኔ መልኩ ብንመለከተውም የወጣለት ሀገርራዊ ክሕደት (Treason) ነው። ቅንጅታውያን በታሪክ ይወቀሱበታል፥ ትርፉም ምን ጊዜም ቢሆን ውርደት ነው። የሀገራችን ልዑላዊነትና ለዘመናት በክብር ተጠብቃ የኖረችው ነጻነታችን ግን ለምንም በምንም ዋጋ አትሸጥም፣ አትለወጥም። የኢትዮጵያ ሕዝብም ሞግዚትነትንም ሆነ ባርነትን አይቀበልም። ልዑላዊነትና ነጻነት ለድርድር ኣይቀርቡም፡- የቀረ ይቀራል እንጂ ልዑላዊነትን በዱቤ አስይዞ በዚያው ፈንታ የሚሸመት የቅኝ ገዢዎች ዲሞክራሲ፣ ወይም የተውሶ ሥልጣኔ፣ በጭራሽ ሊኖር ኣይገባም። ያ ከሚሆን ሳይሠለጠን ቢቀር ይሻላል።

በዚህ ሞግዚታዊ ወይም ቅኝ ግዛታዊ (Colonial bill) ሕግ እና የውጭ ኃይል ተጽዕኖ ምክንያት የዲሞክራሲ ቁም-ነገር ወይም የሀገር ዕድገት ሊመጣ ኣይችልም። ምክንያቱም ዲሞክራሲያዊ ዕድገት እና የሀገር ግንባታ የባሕር ዛፍ ችግኝ ኣይደለም። የአንድ ሀገር ማኀበረ ሰባዊ ባህልና ሥልጣኔ፣ ወይም ሳይንናሳዊ የተክኖሎጂ ዕድገት ከአንድ ቦታ ወደ ሌላው ቦታ አጓጉዘህ በመውሰድ የሚተከል ተክል፣ የጐመን ዘርም ኣይደለም። በተለይ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትና የሀገር ግንባታ ኣብረው በሚካሄዱበት ጊዜ፣ ሂደቱ ታላቅ መስዋዕት የሚጠይቅ፣ ርዥም ጉዞ (Gradual process) ነው። ይህ ነገር በጭፍን ይቻለል በሚል ግትርነት፣ በሞግዚታዊው ሕግ በH.R 2003 ና በውጭ ኃይል በመደግፍ፣ ሥልጣን ይዘው፣ ቅንጅቶች ኢትዮጵያን ያክል የታላቅ ሕዝቦች ሀገር በሰላም፣ አርፈው ለመግዛት የሚያልሙ ከሆነ ተሳስተዋል። አዎ! ከንቱ ሕልም አልሚል፤ <<ሐለሙ ሕልመ ወ አልቦ ዘረከቡ>> የተባለላቸው ለኒሁ ለሐላምያን ሕለመ ከንቱ፣ ለቅንጅት ነው። አዎ! ዓላማ የለሽ ሁሉም ከንቱ ሆኑ።

*የኢትዮጵያ ሕዝቦችም ብቃታቸውን አውቀው አልመረጧቸውም። ዕድል ቢያገኙም ለፖለቲካዊ ኣማራሩ የሚኖራቸው ብቃት እና ታማኝነት (Leadership Quality and integrity) በእጅጉ ኣጣራጣሪ ነበር። በመሆኑም የግብር ኣባታቸው ዔሳው ይቺ ብኵርና ለምኔ ናት በማለት ብኵርናውን ለዕለት ጉርሥ እንደ ሸጣት ሁሉ ቅንጅትም እንዲሁ ሥልጣን ላይ ማንወጣባት ወይም ማንሠለጥንባት ከሆነ ይቺ ኢትዮጵያ ለምናቸን ናት በሚል በግድ የለሽነት ኢ<u>ቃለሏት</u>። በሥልጣን ጥም ሱሰኝነት ታውረው እንሆ አገራችንን ለባዕዳን ኣሳልፊው ሊሸጧት ላይ ታች ሲሯሯጡና ሲዶሉቱ ይታያሉ።*

*እነዚህ የሥልጣን ሱሰኞች ኣስተዋይ ኣእምሮ ቢኖራቸው ኖሮ የሚከተለውን ነገር በተገነዘቡ ነበር። ማለትም፣ የዚህ* H.R 2003 *የሚባለው ቅኝ ግዛታዊ (Colonial bill) ረቂቅ ኣዋጅ አመጣጥና ቅኝ ገዤዎች ወደ ኣፍሪቃ ሲመጡ የተጠቀሙበትን ዘዴ መመሳሰሉ ስለ አፍሪቃ ቅኝ ግዛት ከተጻፉት የታሪክ (Colonial History) መጻሕፍት አንብበው የነጻነትና የባርነትን ልዩነት ለማየት በቻሉ ነበር።*

*ኤውሮጳውያን ቅኝ ገዢዎች ኣፍሪቃን በቅኝ ግዛት ለመቀራመት በመጡ ጊዜ ቀን ኣሳቢዎች እንደ ሆኑ፣ ርህሩሆች እንደ ሆኑ፥ አፍሪቃውያንን ለማሰልጠን እንደ መጡ ነበረ የተሰበከላቸው ስብከት። እንዲሁም የክርስቶስ መስቀል እና መጽሐፍ ቅዱስን አንግበው፣ ውስጠ ተኵላነታቸውን በበግ ለምድ ሸፍነው፣ ጳድቃን፥ ሰባክያነ ወንጌል እና ባሕታውያን መስለው፣ ክርስትናን ለማስተማር በሚል ዘዴ ኸው ብለው እንደ ገቡ ነው ታሪክ የሚያስተምረን። ከገቡ በኋል በተግባር የታየው ነገር ግን በቀጥታና በእጅ ኣዙር በአፍሪቃውያን ላይ ታሪክ የማይሽረው ታላቅ በደል ማድረሳቸውን ነው።*

*በአሁኑ ወቅት ደግሞ እንሆ አገረሸባቸው። ታሪክ ራሷን ትደግማለች እንዲሉ እጅ አዙር ቅኝ ኣገዛዙ ኣላጠግብ ሲላቸው በቀጥታ ተመልሰው መጡ። የራሳችሁ የሆነ ሕግ ማውጣት አትችሉምና በእኛው ሕግ ተገዙ፥ እኛን ብቻ ተከተሉ በማለት ተቆርቋሪና ሕግ አክባሪ ምስለው ዳግም ብቅ አሉ። ለዚሁም* H.R 2003 *የተባለው አዲሱ ቅኝ ግዛታዊ (Colonial bill) ረቂቅ አዋጅ ለማውጣት መከጀላቸው ራሱ ተጨባጭ ማስረጃ ነው። እንዲያውም አዲሱ ቅኝ አገዛዝ ከአሮጌው፣ አሮጌውም ከአዲሱ ምንም ልዩነት የላቸውም፤ ወጮ ቢገለብጡት ወጮ ነው። በጥንቱ ወይም በአሮጌው ዘዴኣቸው፣ አፍሪቃውያንን ሲያታልሏቸው እናሰለጥናችኋለን በሚል ነበር። በአዲሱና በዘመናዊው ዘዴ ደግሞ፣ ዲሞክራሲን እናጐርሳችኋለን በሚል መላምት፣ የእነሱ አፌ ቀላጤ በሆኑት ቅንጅታውያን በኩል፣ አዲሱ ቅኝ አገዛዝ፣ In the name of Democracy and Accountability ዳግም በተሓድሶ እየተሰበከ ነው።*

*የመጀመሪያው ቀጥተኛ ቅኝ ግዛት በሚስፋፋበት ጊዜም ቢሆን እንደ ዛሬው ቅንጅት፣ ለሆድ አደር የወቅቱ ክብረ ቢስ ቅንጅታውያን እንደነበሩ ግልፅ ነው። አዎ! ወንድሞቻቸው አፍሪቃውያንን እንደ እንስሳ እየጐተቱ ለባርነት ኣሳልፊው የሚሸጡ፣ ተባባሪ እና በባርያ ንግድ የተሰማሩ፣ መስተገብራነ እከይ፣ ሆዳምና ክብረ ቢስ ኣፍሪቃውያን እንደ ነበሩ ታሪክ ጨምሮ ያስረዳል። የኢትዮጵያ ሕዝብ ማወቅ ያለበት እውነት ይህ ነው። ቅንጅት ልዑላዊነታችንን በመሸጥ ላይ የተሰማራ ክብረ ቢስ ነው።*